የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ ጥር ፳፮ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ጠባቂነት የወጣ ደንብ

4th Year No. 12
ADDIS ABABA — 3rd February, 1998


CONTENTS


Council of Ministers Regulations No. 26/1998
Zuqualla Steel Rolling Mill Enterprise
Establishment Council of Ministers
Regulations No. ................................ Page 665


COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No. 26/1998

COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF ZUQUALLA STEEL ROLLING MILL ENTERPRISE

The Council of Ministers issued these Regulations pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

   These Regulations may be cited as the "Zuqualla Steel Rolling Mill Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations No. 26/1998."

2. *Establishment*

   1) Zuqualla Steel Rolling Mill Enterprise (hereinafter "the Enterprise") is hereby established as a public enterprise.
   2) The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. *Supervising Authority*

   A body to be designated by the Government shall be the supervising authority of the Enterprise.

ማውጫ


የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፳፮/፲፱፻፺ ዓ·ም
ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች
ምክር ቤት ደንብ ........................................ ገጽ ፮፻፷፭


የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፳፮/፲፱፻፺
ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል ድርጅትን ለማቋቋም
የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯/፩/ሀ/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፳፮/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· መቋቋም

፩· ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" እየተባለ የሚጠራ ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪· ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል።

፫· ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል።

፬· <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በደብረዘይት ይሆናል፤ እንዳስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

፭· <u>ዓላማ</u>

የድርጅቱ ዓላማ የአርማታ (ሪንፎርስመንት) ብረቶችና ስትራክቸራል ስቲል ማምረትና ለገበያ ማቅረብ፣ በተጨማሪም ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን መሥራት ነው።

፮· <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደለት ካፒታል ብር ፪፻፴፫ሚሊዮን፰፻፵፩ሺህ፮፻፺፪ብር·፸፩ (ሁለት መቶ ሠላሳ ሦስት ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከሰባ አንድ ሣንቲም) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፹፫ሚሊዮን፰፻፵፩ሺህ፮፻፺፪·፸፩ (ሰማንያ ሦስት ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከሰባ አንድ ሣንቲም) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።

፯· <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

፰· <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

፱· <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፳፮ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

4. *Head Office*

The Enterprise shall have its head office in Debre Zeit and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. *Purpose*

The purposes of the Enterprise shall be to manufacture and supply reinforcement bars and stractural steel and to engage in other related activities conducive to the attainment of its purposes.

6. *Capital*

The authorized capital of the Enterprise shall be Birr 233,841,692.71 (two hundred thirty three million eight hundred forty one thousand six hundred ninety two Birr and seventy one cents) of which Birr 83,841,692.71 (eighty three million eight hundred forty one thousand six hundred ninety two Birr and seventy one cents) is paid up in cash and in kind.

7. *Liability*

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

8. *Duration*

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 3rd day of February, 1998.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE